# ይቺ ናት የኔ ምድር

(ግጥም)

ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ

**Printed by Fast Imaging,**
**2022 University Ave.**
**Berkeley, California 94704**
**USA**

**Copyright: 2006. Fikre Tolossa**

## ማብራሪያ

ከዛሬ ሠላሣ ዓመታት በፊት፣ ማለትም ኢትዮጵያ ውሥጥ ለይቶለት ርሀብ ከመከሠቱ አስቀድሞ አንድ ኢትዮጵያዊ ወደ አውሮፓ ወይም ወደ አሜሪካ ቢሔድ የትውልድ ሀገሩ መልካም ታሪክና ሐብታም ባሕል የነበርዋት ጥንታዊ ምድር በመሆንዋ በደግ ዐይን እየታየ ይከበር ነበር። ርሀቡ ለዓለም ተገልጦ፣ ዐብዮቱም ፈንድቶ የርሥ በርሥ ጦርነቱም በየአቅጣጫው ተጧጡፎ ከኢትዮጵያ የሚፈልሠውም ሕዝብ በምዕራቡ ዓለም መሠራጨት ሲጀምር ግን ምዕራባውያን ስለኢትዮጵያውያን የነበራቸው አሥተያየት ተለወጠ። ሀገሮቻችንን ወረሩዋቸው ብለው በሮቻቸውን ለኢትዮጵያውያን ከማጥበባቸውም በተጨማሪ ኢትዮጵያን ራሥዋን የድህነት፣ የርሀብና የጦርነት ምሣሌ አድርገው በነዚህ ነገሮች ብቻ የምትታወቅ እሥመሠልዋት። በዚህም ምክንያት በውጭ አገር ያለው ኢትዮጵያዊ በራሡ አፍሮ ማንነቱን በመደበቅ «ሱዳናዊ ነኝ፣ ሱማሌ ነኝ፣ ጃማይካዊ ነኝ፣ አሜሪካዊ ነኝ» ወዘተርፈ እያለ አፉን ሣይዘው ሲያብል ከርሟል። ሐቁን ለመናገር፣ እኔም እውነተኛ ማንነቴን ብገልጽ ጥያቄ እንዳይበዛብኝ በመፍራትና የአዘኝ ቀቢ እንጎች ከንፈር እንዳይመጠጥብኝ በመሥጋት ኢትዮጵያዊነቴን ባልክደውም አልፎ አልፎ ሰባበው አልቀረሁም።

እያደር ግን ነገሩን ረጋ ብዬ ስመረምረው፣ የኢትዮጵያ ዐይነተኛ መለያዋ ጊዜ የወለዳቸው ርሀብና የርሥ በርሥ ጦርነቶች ሣይሆኑ ከዘመናት ጋር ነበር ሆነው የቆዩት ታሪክዋ፣ ባሕልዋና ሙያዋ መሆናቸውን ተገንዝቤ ምንም ችግርዋ ከፅኍሬ የበዛ ቢሆንም በሀገሬ መኩራት ጀመርኩ። ስለዚህም «ይቺ ናት የኔ ምድር» የተሰኘውን ረጅም ግጥም ጽፌ የሀገሬንና የሕዝብዋን ታሰቅነት ለማንፀባረቅ ተነሣሣሁ።

በዚህ ግጥም ውስጥ፣ ኢትዮጵያ ለዓለም ሥልጣኔ ያበረከተቻቸውን ቁምነገሮች ከማተቴ በተጨማሪ፣ አሁን ኢትዮጵያን የሚንቅዋት አንዳንድ ምዕራባውያን፣ ምግባረ-ሠናይነትን እና ሰብዓዊነትን ከእሷ ሊማሩ እንደሚችሉ ጠቁሚያለሁ። ይህንንም ለማድረግ የበቃሁት በማለዳ ከኢትዮጵያ ወጥቼ ለበርካታ ዓመታት በምዕራቡ ዓለም በመኖሬ የሀገሬን ሕዝብ ሥነምግባርና ሰብዓዊነት ከምዕራባውያኑ ጋር አነፃጽሬና አወዳድሬ የኛዎቹ እጅግ የላቁ መሆናቸው ስለተከሠተልኝ ነው። እድሜ ልኬን የኖርኩት ኢትዮጵያ ውስጥ ቢሆን ኖሮ የሕዝቦቼን ጉድለት እንጅ መልካምነታቸውን ለማጤን ባልቻልኩ ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ የኖረ ሰው ሌላ ማወዳደሪያ ሕብረተሠብ ስለሌለው ሕዝቦቹ ሠርክ የሚፈጽሙትን መልካም ነገር በዘልማድ እንደተራ ጉዳይ ይመለከተዋልና። ሕብረተሠብ ከጥፋቱ ታርሞ እንዲሸሻል ጉድለትን መጠቆም አብዛኛውን ጊዜ የአንድ እውነተኛ ከያኒ አደራና ሃላፊነት ቢሆንም፣ ሁልጊዜ ጉድለቱን ብቻ ፈልፍለው እያወጡ እራሥ እራሡን ቢቀጠቅጡት ያ ሕብረተሠብ በማበብና በማደግ ፋንታ ይቀጫል። የሕብረተሠቡን መልካምነትና የሕይወቱንም ብሩህነት እየፈለጉ አልፎ አልፎ ማሣየት ሕልውናውን የሚጥም ያደርገዋል። የኢትዮጵያን ጉድለት ሁላችንም እናውቀዋለን። እስቲ መልካምነትዋንም ሸተን አግኝተን ለእድገትዋ ሥሬ-መሠረት እናድርገው።

በአፍሪካ፣በአሜሪካና በአውሮፓ ውሥጥ ተቀምጬ፣ በረጅም ዘመናት ትምህርትና በተሞክሮ ያካበትኳቸውን ግንዛቤዎችና ትዕዝብቶች በዚህ ግጥም ውሥጥ ከማካተቴም ሌላ ከትንሽ ልጅነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ ከትኩቼ ያሰደግኩትን የሥነ-ግጥም ሥጦታዬን ተጠቅሜበታለሁ። ይህ ግጥም፣ አሁን በሀገሩ ዕጣ ያፈረውን ግለ-ሠብ በሀገሩ ታላቅነት ልቡ በኩራት ተሞልቶ በራሱ እንዲተማመን ያደርገዋል ብዬ አምናለሁ።

«ይቺ ናት የኔ ምድር» የተሰኘው ይህ ግጥም

ከፍሬ-ሐሣቡ በተጨማሪ የአንዳንድ የቆዩ ልማዶቻችንን እናቶቻችንና አበቶቻችን ዕለት በዕለት የተጠቀሙባቸውን የመንፈሣዊና ሥጋዊ ነገሮችን፣ የሃይቶቻችንና የወንዞቻችንን፣ እንደዚሁም የተረሡትን የእጽዋታችንና የአእዋፋችንን የሌሎችንም እንሥሣቻችንን ስሞች በመዘርዘር እነዚህ ሁሉ ተዘንግተው ትቢያ ሆነው ሣይቀሩ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲተሰለፉ ይጣጣራል። ይህ ግጥም እ.ኤ.አ ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ በጀርመን ሬዲዮ ሲተሰለፍ አድማጮች እንዳገና መስማት እንፈልጋለን ስለሉ በተከታታይ ብዙ ጊዜ ተሠምትዋል። የብዙ ኢትዮጵያውያንን ሞራልና ኩራት በማነሰሰቱም በርከታ የሀገሬ ሰዎች የምሥጋናና የአድናቆት ደብዳቤዎች ለኔና ለሬዲዮ ጣቢያው ከመጻፋቸውም በተጨማሪ የግጥሙን ግልበጭ እንድልክለቸው ጠይቀውኝ ነበር። ይህ ግጥም በኢትዮጵያ ያሉትን ወገኖቼን ብቻ ሳይሆን በውጭ አገር የሚገኙ የሀገሬ ሰዎችንም ልብ ሊነካ ችሏል።

«ይቺ ናት የኔ ምድር» በተባለው በዚህ ግጥሜ ውሥጥ ስለምዕራባውያን ስናገር የምጮክርባቸውና እነሱን ያጠቃሁዋቸው መሥጹ ከታየሁ አጠቃቂ «የአልሞት ባይ ተጋዳይነት» እንጂ የበግፍ ገዳይነት አይደለም። በዳፈናው እንነጋገር ካልን፣ እያንዳንዱን በዓለም ላይ ያለውን ሰው ቀለሙን ሣለይ ሰፈትረው እማጣራለሁ። በዚህ ጉዳይ ላይ አቋሜ ጽኑ ነው።

እ.ኤ.አ ታኅሣሥ 27 ቀን 2004 ዓ/ም
ሽሊሆ፣ ካሊፎርኒያ

ይቺ ናት የኔ ምድር

ድሮ፣ ድሮ፣ ድሮ፣...እናት-ምድር አራሥ ልጅ ሆና
በሎርቃነትዋ ወራት ወገብዋም እንኳ ሰይፀና
ጊዜ ማሙሽ ሣለ ተወልዶ ገና
እምበቃቀስ ሆኖ ሲበልለት «ዳዴ ብሩ ገልና»
ከዋክብት በሠማይ ተረግዘው በሽልነታቸው እንደተቀመጡ
ገና ውጋጋን-ደም ሣሉ፣ ተሽልቀቀው ተንበግቡገው ሰይወጡ
ገና ያኔ ገናና የነበርሽ የሀገሮች በኲር፣ የብሄሮች አድባር
ከነሜሦጵታምያ፣
ከነባቢሎኒያ ከነግብጽ፣ ከነቻይና ከነጽርዕ እኩል የከበርሽ ኢትዮጵያ
የሕልውናሽ አሻራና ዝናሽ ያልተሠራጩትን ያህል ከዛንዚባር እስከ ኑብያ
ከማደጋስካር እስከዘይለ ከምሥር እስከሒንድያ ከየመን እስከዐረብያ፣
ዛሬ የምትልሺው የምትቀምሺው ኩርማን እንጀራ አርሮብሽ ዋ! ኢትዮጵያ
ጉሮሮሽ በጥም ተቃጠለ ውሃ እጥተሽ አንድ ኩባያ
ዛሬ ቡትቶ ብርቀ ሆኖብሽ ግንድሽን ጥለሽ ሆንሽ መሰሰቂያ
ዛሬ በተትረፈረፈው ዓስም ጠኔ እየቆሰሽ ሆንሽ ያዳሜ መሣቂያ
ዛሬ የፐለኔታችን ምጽዋተኛ እንቺ ሆንሽ ቢጤ የሌለሽ እኩያ
ዛሬ ያንቺ አጽም በየሜዳው ረገፈ፣ ወደቀ እንደፋንድያ!---
የእንቁጣጣሽ እለት በመሥኩ፣ በስምስሙ
ሣዱለ ልጆችሽ ቂጤማ እየነቀሉ፣ አበባ እየለቀሙ
«አበባዬ ሆይ አበባዬ
ርግፍ በሸማዬ
አበባ ሰሽ፣ ሰሽ፣ ሰሽ
ሊበላኝ ነበር የባብ ውሺ።
አበባ ሰሽ በየዱሩ
ባልንጀሮቼ ወልደው ዳሩ።
አበባዬ ሆይ!
ስምስም

ባልንጀሮቼ ቀሙ በተራ
እንጢጥ ሠብሬ ቤት እስክሠራ
እንቧን ቤትና የለኝም አጥር
እደጅ አድራለሁ ክከብ ስቆጥር»
እያሉ በሮለሉበት ቀዬሽ፣ ዛሬ ተከንችረው ሁሉም
እጽማቸው ወድቆ ተቆስ፣ ጋይቶ ጢፈውም ቅጠሉም።
ልጃገረዶችሽ አክሊለ–ጽጌ አድርገው እየዞሩ
ሸበላዎችሽም የመሥቀሉን ደመራ እየዘሩ
«ኢዮሐ አበባዬ!
መሥከረም ጠባዬ
አበባዬ አበባዬ ሆዬ!
መሥከረም ጠባዬ» እያሉ እንዳልዘመሩ
ደመራውን በዘሩበት ሜዳ ፍግም ብለው ቀሩ።
ሠርግ ደግሠሽ ዳሥ ጥለሽ፣ የልጆቼን ዓለም ዐያለሁ ብለሽ
ልጆችሽን ወግ ልታደርሺ መርቀሽ፣ ዘይነሽ፣ ኩለሽ
እልልታሽን እያቀለጥሽ አእላፍ እድምተኞችን ባበላሽበት ሥፍራ
በተዘፈነበት፣ በተጨፈረበት፣ በተረገጠበት ዳንኪራ
ዛሬ የልጆችሽና የልጅልጆችሽ አስዘራን ተዘራ።
እያቶችሽ ቅድመአያቶችሽ፣ ልጆችሽም ተወልደው ያደጉበት ቤት
በዘመድ አዝማድ በእንግዳ፣ ጢም ይል የነበረው በጎረቤት
በቀልድ፣ በጫጫታ በእልልታ፣ በሣቅ በሆታ እየደመቀ
ቅመማ ቅመሙ እየሸተተ፣ ጭሱ እየጨሠ፣ እሣቱም እያሞቀ
ወተቱ፣ ሥጋው፣ ጠጁ፣ ወይ ጠላው ተትረፍርፎ ሞልቶ እህል
ሕያዋን ነፍሣት በጥጋብ አንድ ዘመንም ቢሆን ያልተንበሸበሹትን ያህል
መቃብር የሆነ ይመሥል ዛሬ ቤቱ ተደፍኖ እና ሆኖ
በሩ ከውጭ እንደተቆለፈ፣ ዐይጥና እባብ ይፈነጩበታል እርገውት ጉረኖ።

ሠብሉ ሰማይ እየቧጠጠ፣ ንፋሱ እየዘመረ የሐጋይ ዜማ
ወጣቶችሽ እየከመሩ ምርቱን በገቡበት እውድማ
ዛሬ ጥሪኝ እህል ተቸግረው እዛ ወድቀው እንደ ዋዛ



እሬሳቸው ተጋዝ በቃሬዛ።
ልጆችሽ ውሃ እየተራጩ ራቁታቸውን የዋኙባቸው ወንዞች ተንነው
እጽማቸው እዛ ተበተነ በጥማት አርረው በግነው።
እረኞችሽ ዋሽንት እየነፉ ፀሐይ ሲሞቁ
ከብቶችሽ እያመሠኩ አረንጓዴው ላይ እንዳልበረቁ
ዛሬ አረንጓዴው ጥላሸት ሆኖ ጠቁሮ
የከብቶችሽ ቅሬት አጥንት ይታያል ተከምሮ።

ጉብሎችሽ ዱላ ይዘው ጅራፍ እያጮሁ በቡሄና በዐውደመቱ ሆያሆዬ
እየጨፈሩ
«እከሥቴ ቤት እለኝ ለከት፣ እንቴ ቤት አለኝ ለከት» እያሉ ከቤት ቤት
እየዞሩ
እዛ ማዶ ጭስ ይጨሣል
እጋፋሪ ይደግሣል
ያንን ድግሥ ውጪ ውጪ
በድንክ አልጋ ተገልብጪ
ያች ድንክ አልጋ አመለኛ
ያለንድ ሰው አታስተኛ
የኔማ እመቤት የፈተለችው
የሸረሪት ድር አስመሰለችው
ሸማኔ ጠፍቶ ማርያም ሠራችው
ለዛች ለማርያም እዛ ኑሰት
ዓመት ተመንፈቅ አለቀለት።
ለዝና ብሎ የሠጠኝ ሙክት
በለጭማ ነው ባለምልክት
መስከረም ጠባ ያንን ሣነክት።
ክበር በስንዴ ክበር በጤፍ
ምቀኛህ ይርገፍ።
የነጭ ጤፍ ዘፋፋ
የወለዷት ይፋፋ»

ብሰው መርቀው የሠበሠቡትን ዳቦና ሥጦታ እየተከፋፈሉ
ሰለጥጋብ እየዘመሩ እንዳልጠገቡ፣ ሆያሆዬ በጨፈሩባቸው ደጃፎች ሁሉም
ተከነበሉ።
ጡቶችሽ ቀልጠው ተሟጥጠው ባዶ ከረጢቶቻቸው ብቻ ተንጠልጥለው
ዐራዎችሽ ያንን ይመጠምጣሉ ድብን እርር ብሰው ተቃጥለው።

በልጃገረድነትሽ ወራት ከባልንጀሮችሽ ጋር እጊጣችሁ
በበዓሉት ቀን በየሜዳው ደንኪራ እየረገጣችሁ
ዘንጎች በያዙ ጎረምሦች ተከባችሁ እያወካችሁ
ደስ ከሚል ዋችሁ ጎረምሦች ዘንጎች ላይ ሎሚውን እየሠካችሁ
«ንሆሎ ንሆይሆለሎ
ንሆሎ
ደኸ የማነው
ንሆይ በል
ጉተናው ዋሽ
ንሆይ በል
ሲሸሽ ዐየነው
ንሆይ በል
ጌሽ ለጌሽ
ንሆይ በል
ንሆይሆለሎ»
እያሳችሁ እየዘፈናችሁ ያጣጣማችሁበት መሥክ ላይ የእፍሏ ፍቅርን እውሳ
ዛሬ በድናችሁ እንደዐዛባ ተጣለ አፈር አልባሽ አጥቶ እየተጉሰሰ።

እልባብ እልባብ እጡንበር እጡንበር ይተነፍሥ የነበረው ዐየርሽ
ብርጉድ ብርጉድ ጠጅሣር ጠጅሣር ያውድ የነበረው ዳር ድንበርሽ
ሐሬቲ ሐሬቲ፣ሊባንጃው ሊባንጃው ደሸት የነበረው አፈርሽ
ናዕናዕና ናዕናዕ፣ ከሙን ከሙን ይል የነበረው ምድርሽ
ዛሬ ደከረፋል ጥምብሽ፣ እጥተሽ ቀፍሮ የሚቀብርሽ።
እንደጠበል እየቀዘቀዘ ነፍሥ ደፈውሥ የነበረው ንፋሥሽ



ዛሬ ቃጠሎ ወሏፈን፣ የሚተነፍግ የሚያፍን ነው እሥትንፋሥሽ።
በውጋጋን በብልጭታ እንደሰጸደለ ሠማይሽ፣ መብረቅ እየበረቀበት
የነጎድጓድ ድቤ ከበሮ እንዲያ እንዳልተደለቀበት
እዝእርትን የሚያረሠርሥ ዝናብ ከውሥጡ እንዳልተንደለደለበት
ሠራ ዊተ-ሠማይ እያሸበሸበ ጮቢ እየመታ እንዳልፈነጠዘበት
ዛሬ ሠመያዊው ነብዞ ኑግ-ቀልሞ፣ የመቃብር ጭርታ ሠፍሮበት
ውርበው በዋር ተተከቶ ዕሉን ደዌ ረጭቶበት
ሽቱ ይናኝ የነበረው ዛፍ ሁሉ ወይቦ ደረቀ እንደ ዘበት።
ተራራው ተተርትሮ እንደፍም ተንደርከከ፣ እንደገና ደቦ ተሸንሽኖ
መሬቱ ተሠነጣጥቆ ተገማምሦ፣ የገሃነም ረመጥ ሆኖ
ጀምበርዋ ነዲድ ነፍጥ እየተፋች እራ ዊቱ ተጠብሦ አረረ
እግር ማረፊያ አጥቶ ተኩማትሮ እየጨሠ ተንጨረጨረ!
ኢድን ያልነበርሽ የመሥል ልምሏሜሽ ምድረ-ገነት
ዛሬ ምድረ-በዳ ሆንሽ ኢትዮጵያ፣ የቃጠሎ የርሀብና የጦርነት እብነት።

ተጎናጽፈሺው እንዳልነበር ሠማይ ጠቀስ ሰንደዶውን፣ ጨፈውንና
ቄጤማውን
የተቆሰዘመ ወለሹን፣ ጃፍጃፉንና ሠርዶውን፣ ዋዋቴውንና ዋኽርማውን
ጓሣውንና እሰታውን፣ግራምጣውንና ኩመሩን፣ እንሥሳልና እክርማውን
በርሠነቱንና ርጎፍቱን፣ ሸነቱንና እሸቴውን፣ ዳማከሴውንና እሉማውን
ያልሰበሺውን ያህል፣ ጦስኝና እንሰስሳውን ፣ በሶብሰና ጤናዳሙን
እጥበሩንና ጠጅሣሩን፣ ሀሬቲውንና እልባቡን፣ ናዕናዕውንና ከሙን
ያልፈነጩብሽን ያህል እነዐዳይ፣ እነጎሚት፣ እነቀያቴ፣ እነጽጌረዳ
ሰመያዊ፣ ሐምራዊ፣ ወርቅ-እሥተኔ፣ ወይንጠጅ፣ ነጭ-ፀዐዳ
ቀይ፣ ብጫ አበባ መሥክሽ ላይ እንዳልፈነዳ
ሐመልማልነትሽ ወድሞ ዛሬ ሆንሽ እሉ ባድማ፣ የወሏፈን ምድረ-በዳ!
ከሥሎ ጥዱ፣ ዝግባው፣ ዐርዘሊበኖሱ፣ ዘጲው፣ እብኖሱ፣ ፍልፍሌው፣
መናኄው፣ ሸሳው፣ ቢርቢራው
ጅብራው፣ ባበው፣ ግራሩ፣ ነቢሳው፣ ጥጡ፣ በሰሠ፣ ባሕርዛፉ፣
እዝጋሮው፣ እንቡሉ፣ ቍርቍራው

ቀለዋው፣ ወይናግፍቱ፣ ከሸሽለው፣ እንቃው፣ በደኖው፣ በሉጡ፣ በምበው፣
ደሬው፣ እጋሙ፣ ወይራው
ወርከው፣ ዋንዘው፣ እንክ ዩ፣ ከሽሙ፣ ሠፈርጃሉ፣ ጊሽማው፣ ቀጋው፣
ፍየለፈ ጄ፣ ድማው
ቀንጠፋው፣ ዋሰማው፣ ቶማጨው፣ እምበሽኩ፣ ብርጭቁ፣ ሎሚው፣
ፓፓዩው፣ ደቅማው
ብርቱካ ኑ፣ ሙዙ፣ በጢሖ፣ እንጆሪው፣ ዘይቱ ኑ፣ ከኩ፣ መንደሪ ኑ
እንዘሪዩው፣ ብበናው፣ ቀልቋሉ፣ ማንጎው፣ አናናሉ፣ የወፍቶሎው፣
እውጡ፣ ሮማ ኑ
ሸንከራአገዳው፣ ወይ ኑ፣ ዝተሬው፣ ማሽለው፣ ዳጉሣው፣ ሽምብራው፣
ሲናሩ፣ በቆሎው
በርማሸለው፣ በለቄው፣ አደንጓሬው፣ ጤፉ፣ ምሥሩ፣ ሠሊጡ፣ ተልበው፣
ኑጉ፣ ዳንጎሎው
እንዳሪያው፣ በቢሎው፣ ጌሾ–ግንቢሩ፣ ሰናፍጨ፣ ፎሠሊያው፣
እንበዲያቱ፣ አቶሰሉ፣ እበቡቴው
ደሞዩው፣ በንዴማናው፣ ፀብሹ፣ ሉፋ፣ ጎንደሬው፣ አየሩሲው፣
በሪያሰደዴ፣ ግንበቴው
አልበቀሰብሽ ይመሥል ቀሥጣውና በንዴራው፣ ነጭና ቀይ ሽንኩርቱ፣
ያበሸውና ጥቀሉ ጎመን፣ ቀይ ሥሩና ኩሩንበው
በሕሮውና ድንቹ፣ ምጣጢሱና አደንከሬው፣ ቲማቲሙና ሠለጣው፣
ቃሪያውና ዱበው
እጽዋትን አጋይቶ ደግአመድ የሚያደርግ ጎሞራ
ዛሬ እንቺን አረገሽ እሱኝ የመሥቀል ደመራ!

እነወረቤ፣ እነዋነሲ፣ እነሥሪት፣ እነርግብ፣ እነጪ ረበ፣አልቀዘፋበት
ይመሥል ያንቺን ሰማይ
እነጉራማይሌ፣ እነድርጭት፣ እነእንድርማሚት፣ እነጃንጄሰቴ፣
እነፀብርል፣ እነወማይ
እነዋሪ፣ እነሽመለ፣ እነጎረጥ፣ እነቢጨ፣ እነድንቢጥ፣ እነጉትዩ፣
እነመሥቀልወፍ፣ እነነጎዴ፣ እነመቄ

እነቡያ፣ እነብቲ፣ እነግዎበ፣ እነጭራ፣ እነአምበሳ፣ እነግሪሣ፣ እነደበ ኔ፣
እነወገበ፣ እነዴንቄ
እንዳልከነፋበት ሖዋሽን እነሐሲዳ፣ እነራዘ፣ እነርኩም፣ እነንሥር፣
እነሸተሌ፣ እነሸለቅ፣ እነእገዳሠበር
እነግልገልእንሣ፣ እነጀፌ፣ እነሚሰ፣ እነየሎሥ፣ እነኸብሪ ሆነው
እንዳል ነበር
እነከርከሩሜ፣ እነመሬቡ፣ እነፀመቴ፣ እነሠጎን፣ እነጎሚ፣ እነጭልፊት፣
ሁሉ ጠፍተው እነቁራ
ሠለጠ ኑብሽ እሉ እነዘማ ኑም፣ እነፀፍርአይገበ፣ እነዘማችአሞራ!

ነድደው እነቁርዩ፣ እነይብራ፣ እነዝዩ፣ እነአቁሥጣ፣ እነከራ ድርዮን፣
እነጺልቃን፣ እነብሄሞት፣ እነበ ቡሬ፣ እነወንዘሪጭ፣ እነሣቢሣ
እነምኽልግ፣ እነግንቡል፣ እነሎምቢ፣ እነደፎጭ፣ እነወጊት፣ ከቀሰይሽ፣
ከወንዝሽ ዳረቀ እነነበሪፀሣ።

ፍየሎችሽ እነጠራጠርማ፣ እነሴደርማ፣ በጎችሽ እነበሖ፣ እነዘገሲ፣
እነዳንግሊ፣ እነበለጭማ
በሬዎችሽ እነሲረን፣ እነበቃ፣ እነባቤለ፣ እነእሻልማ፣ እነሻበ፣ እነቡሬ፣
እነጓንጉል፣ እነበሩ፣ እነበርማ
በቅሎዎችሽ እነዋርዴ፣ እነግራጫ፣ እነጪበር፣ እነሸከለ፣ እነሲሙና፣
ፈረበችሽ እነቡሎ
እነዳማ፣ እነእሻል፣ እነዴሪ፣ እነበራ፣ እነዳለች፣ እነሸሌ፣ እነአምበሳይ፣
እነጉሎ
ዶሮዎችሽ እነሲውሲዋ፣ እነዘሪምበ፣ እነሻሻቴ፣ እነገብስማ
እነወሠራ፣ እነልበ–ዳለቻ፣ እነቀይዴልዴም፣ እነዛጎልማ፣ እነቆቅማ

የዱር ፀውሬዎችሽ እነዝሆን፣ እነአውራሪስ፣ እነወደቢ፣ እነአንበሣ፣
እነከሪከንድ፣ እነአንበራ ሌ
እነዋሊያ፣ እነድፋርሰ፣ እነደበ፣ እነእጋዘን፣ እነቆራፈረሰ፣ እነጎሹ፣
እነኤልሞሌ

እንቀጢኔ፣ እንፈቅ፣ እንሰሳ፣ እንገረሚ፣ እንዴብሎ፣ እንዘብራ
እንብሖር፣ እንምዳቿ፣ እንሀየል፣ እንዋሊያ፣ እንዳርጋንበሣ፣ እንደንጎሎ፣
እንቶራ
እንሜዳእሀያ፣ እንከርከሮ፣ እንኤብ፣ እንጪዋ፣ እንገመር
እንአንሹ፣ እንጉራዘ፣ እንፍልፈል፣ እንጢንቸል፣ እንግሥሳ፣ እንትግሬት፣
እንአነር
እንቧን እንቺን ሊቤዠሽ ነፍሳቸውን ማትረፍ አቅቷቸው!
እንደአሸሮ አርረው ቀሩ እንቺን ያጠቃ እጥቅቷቸው
እንኹብና ወበሸግ ኔ፣ እንእውጪ ብቻ ተረፉ እሱ በሱ ሠምሮሰቸው፤
ነገሩ ሳንቺ ተበሳሽቶ እነሱ እምሮባቸው።

ኃይቅ ወንዞችሽም ሳም አሰኝ በሰማይ ሆ ኑብሽ እንጆ፣ ከዚህ ከምድር
ሊያርሱሽ
ወተታቸውን በጉሮሮሽ ሲያንቆረቁሩ አልቻሉም ሲያረሠርሱሽ።
ሰም ሆ ኑብሽ አንጆ አዳበይ ዥረቶችሽ አልደረሱልሽም አልበጁሽም
እንመገር
እንአዋሽ፣ እንፋፈን፣ እንሼቤሊ፣ እንአሞ፣ እንጄጄሳ፣ እንበሮ፣ እንዴበር
እንዳዋ፣ እንወይብ፣ እንጆብ፣ እንመረብ፣ እንተከዜ፣ እንገናሊ፣ እንአንገር
እንጊቤ፣ እንሸሳ፣ እንጣና፣ እንሰንጋኖ፣ እንሃይቅ፣ እንጪው ባሕር፣
እንአባያ
እንጊሎ፣ እንዳቡበ፣ እንጫሞ፣ እንአዋሣ፣ እንአቢያ፣ እንሀረማያ
እንአቅበ፣ እንጎጆብ፣ እንአትባራ፣ እንበሰሳ፣ እንዲንደር፣ እንዣዋይ
እንረሃድ፣ እንእንግረብ፣ እንጋሽ፣ እንባርከ፣ እንአንሰበ፣ እንአደበይ
የባዕድ በርሃን ሲያሰመልም የወንዞቹ አባትም ሳንቺ አልፈየደሽ አበይ።

አዎን ዛሬ ፀደ በርሃ ሆንሽ ኢትዮጵያ ሠርክ ፀበል እንዳልዘነበብሽ
ዛሬ የመጨረሻዋ ሰማኝ ተባልሽ ጣረሞት የሚያዠብብሽ
ዛሬ ስምሽ መሸቀጫ ሆነ ሁሉም ምጽዋት የሚለምንብሽ
ዛሬ የጋዜጠኛ ሲሣይ ሆንሽ ፣ እዛኝ ቅቤ እንጓች የሚዘበትብሽ።
ኢትዮጵያዊነት የሚያከራ ጥንት የሚያስከብር እንዳል ነበረ



ዛሬ እንደሚያሣፍር ነገር፣ እንደሚያዋርድ ተቆጠረ።

«አሀ! ኢትዮጵያዊ ነህ? በጣም ድሀ ነች አገርህ
ሕዝብህ እጅግ ርሀብተኛ ነው፣ አምልጠሃል አንተ እዚህ በመኖርህ»
ይሰኛል ምደረ-ነጭ ከመሐይመ እስከ ምሁሩ
ኢትዮጵያ በርሀብና በድህነት ብቻ የምትታወቅ ሆነና ነገሩ፤
አዎን፣ እዎን ብዬ አልፋለሁ ሲታከተኝ መከራከሩ።
ኢትዮጵያዊነት የሚያኮራ የሚያስከብር እንዳል ነበረ
ዛሬ እንደሚያሣፍር ነገር፣ እንደሚያዋርድ ተቆጠረ።
ኢትዮጵያ በርሀብና በድህነት ብቻ የምትታወቅ ሆነና ነገሩ
አዎን፣ እዎን ብዬ አልፋለሁ ሲታከተኝ መከራከሩ።
ሠምቼ ሠምቼ ግን ሲበዛብኝ፣ ሐቁን እመሠከራለሁ
ድንቁርናቸው እያናደደኝ ትዐግሥቴ አልቆ እመራለሁ
የሀገሬን እውን ማንነት ለማብራራት እጥራለሁ።
እናንተ አሁን ብትረሱትም፣ ጀርመንና ፈረንሣይ፣ እንግሊዝና ሩሲያ
ቀድሞ ተርበው እንደነበር፣ ዛሬ ተርበሰች ኢትዮጵያ።
ግን ዘለዓለም የሚቀይ አይምሠሳችሁ ርሀብዋ
ደፋክ ርሀብ ብቻ አይደለም የኢትዮጵያ መለያዋ
የእናንተን ሊያሥንቅ ይችላል፣ በሕልዋ፣ ታሪክዋና መልያዋ።
እናንተ ሕዝቦች ብሔሮች ተብላችሁ ሣይታወቅ መፈጠራችሁ
ቤት ምን እንደሆነ ሳታውቁ ሣላችሁ በዱር እየኖራችሁ
እሷ መንግሥት መሥርታ ደንብና ሕግን በማስከበር
ሕዝቧን በሥነሥርዓት፣ በፍትሕ ታስተዳድር ነበር።
እናንተ እሕዛብ አረማውያን ሆናችሁ፣ ጣዖት እያመለካችሁ
ርሥበርሣችሁ ስትፋጁ በነገድ በጎሣ ተከፋፍላችሁ
ኢትዮጵያ ግን የመለከትን ሕግ-እሪት ተከትላ
ከናንተ ቀድማ ሠልጥናለች፣ ኋላም ክርስትናን ተቀብላ።
የራሥዋን የቤተክህነት ሥርዐተ-አምልኮ ደንግጋ
ከናንተ እንዳች ነገር ሣትበደር፣ የነፍሥ ሆነ የሥጋ።
ከጽርሀ አርያም የወረደ ማኀሌትዋ፣ ለሰው ልጅ አእምሮ የረቀቀ

ከሥጋ ስባሽ ጉሮሮ ያልወጣ፣ እውነትም ከመስከት እንደበት የፈለቀ
ግዕዝ፣ አራራይ፣ ዕዝል፣ ድጓ፣ ፅመ–ድጓ ለሚያዳምጠው በየተራ
መንፈሥን ከእኩይ ዓለም ነጥቶ፣ ወደሰማየ ሰማያት የሚጠራ
ሰንቧን የመሰኮትን ፍጡር፣ የሠይጣንን ልብ የሚያራራ።
እንበቸው እሥቲ ከገበህ የማኅሌቱን ግጥሞችና የዜማ ምልክቶቹን፣
ቅናትና ደረትን
ድፋትና ይዘትን፣ ርክርክና መንገድን፣ ቁርጥና ጭረትን
ገና ያንተ መዝሙሮችና የሙዚቃ ምልክቶች ባይደረሱ ሠበት መቶ ዓመት
የኖሩትን
ያንተ ማኅሌታውያን እንቅልፋቸውን ሲሰጡ የኔዎቹ ነቅተው
የፈጠሩትን።
ቋንቋዬ ጥልቅ ነውም ከልክ እንመርምረው፣ እንመዝነው ከስህ ቅኔ
ሰምና ወርቅን ውሥጠ–ወይራን፣ አፍራሽንና ኅብርን፣ ያውቃል ቋንቋህ
እንደየኔ?
የከበ አስመስሎ እሳይ አውጥቶ፣ መልሦ እታች አውርዶ ይከሠከሣል?
አሁን በድሉ አበቀይሞ፣ ወዲያው እንጃት እርሦ ይከሣል?
በራሥጌ እንደዝሆን አተልቆ በግርጌ ያሣንሣል እንደ ትንኝ?
ከሰይ ዋሽቶ ከውሥጥ እውነት ሊናገር፣ ይችሰል ያንተ ግጥም ሰንኝ?
ወታደሩና ገበሬው፣ ነጋዴውና እረሆው፣ መሐይሙና ደብተራው፣ ንጉሡና
ሰማኙ በሊቅ እስከ ደቂቅ
እንደኔ ሕዝብ ያንተ ሕዝብ ቅኔ ይቀኛል? ሁሉ ገጣሚ ሁሉ ከያኒ
ነወይ ረቂቅ?
እንደኦሮምኛና ትግርኛ ተናጋሪ ወገኖቼ ወዝና ጣዕም አለው ያንተ
ንግግርና አነጋገር?
እንደኔ ወገኖች ቋንቋ ጥበብ በተሞሉ ጥቅሦች፣ ተረቶችና ምሣሌዎች
አሸብርቋል የወገኖችህ ዐርፍተ–ነገር?

የራሥዋ ፊደሰት የነበራት ኢትዮጵያ የራሥዋ የብዕር ሰዎች
ባለቅኔዎች፣ ፈላሥፎች፣ ባለታሪኮች፣ ባለመድሐኒቶች፣ ዜማ ደራሲዎች
ብርቅዬ እንጥረኞች፣ ብልሃተኞች ባለእጆች፣ ጣታቸው ወርቅ ሸማኔዎች



ሕዝቦችዋ የሐርነት ምሣሌዎች፣ ዝንተ–ዓለም ነፃነት አፍቃሪዎች
እጥንቴ ሣይከሠዙሥ ክንዴን ሣልንተራስ እልገዛም ባይዎች
የዛሬን እያርገውና የመንገደኛ እግር ያጥቡ የነበሩ ትሁትዎች
አንድ እንጀራ ሰሥር የሚከፈሉ ሰጋስ ሩኅሩኅዎች
እልጋቸውን ለእንግዳ ለቀው መሬት የሚተኙ እንሥፍሥፍዎች
ይኸውልህ እነዚህ ናቸው የኔ ወገኖች! ይኸውልህ እነዚህ ናቸው የኔ
ሕዝቦዎች!
ከግር ጥፍራቸው እበከራሥ ፀጉራቸው
እምሏክ እንቅልፍ እጥቶ ከሽዋ የሠራቸው
የፍጡራን ናሙና እርጎ ከያዴነቱ ያጠራቀማቸው
የሰውን ልጅ ዘር ለሚያጠኑ ብርቅዩ ከምችቶች ያረጋቸው
ኩሽን፣ ሲምን፣ ክምን፣ የስብዕ ዘረ–ግንድን
የኦሮሞ፣ የኩናማ፣ የአማራ፣ የአፋር ነገድን
ወይጦን፣ ሱማሌን፣ ትግሬን፣ ፈሰሻን
ሣባን፣ ዮቅጣንን፣ አገውን፣ ቅማንትን፣ ሽናሻን
ኧረ ሥንቱን! ሁሉን በያይነቱ የምታሰኅበኝ የሕዝቦች ቤተመዘክር
እሥዋ ራሥዋ ዩኒቨርሲቲ ቋንቋን ለሚሠነጣጥር
ብዛቱ የበዓሉ፣ የልደቱ፣ የሠርጉ፣ የሞቱ፣ የማይደገም በምድር
ዕጡብ ድንቅ ሰበሕል መምር
የእንሥሦች ሥረ–ምንጭ እንሥሣን ለሚመረምር
የእጽዋት እጸደ–ገነት እጽን ለሚበረብር
የኪነ–ጥበብ ግምጃ ቤት ኪነትን ለሚቆፍር
የቃል–ሥነጽሑፍ ጎዳ፣ አፈ–ታሪክን፣ ተረትን፣ ምሣሌን፣ ዘፈንን
ለሚተረትር
የሕንፃ የሐውልቶች እምብርት ከርሠ–መሬትን ለሚሠረሥር
የዓለም ታሪክ ቅንጮ ታሪክን ለሚያብጠረጥር
የምድርን ገጥታ ለሚገመግም የሦሥት ዕድሜ–ልክ ሚስጥር፣
የሕዝቦችዋ ቀለም ከጥቁር ሊሊት እበከቸከሌታ፣ ከቀደዳማ እበከ ወርቀዘበ
ደማስ ኅብር
ሁሉ ቆንጆዩዎች፣ ሁሉ ሸሞንሟኖች፣ የውበት መጋዝኖች፣ በሕያቸው

የቱሪሥት ዐይን የሚያሠከር
የተሸለመለሙ አልበሣት፣ የዜንዋ የዘመናይ ጌጣጌጥ መደብር
የሥክሥታዋ እጹብነት፣ የሽብሽበዋ ድንቅነት፣ የጦቢዋ አይገኜነት፣
የዳንኪራዋ ሥልት ቅንብር
ለትንግርት፣ ለሰንቲክነት የተሠራች፣ ለወዳጅዋ ጋሻ፣ ለጠላቷ
መቅሠፍተ—በትር
ይኼውልህ ይቺ ናት የኔ ምድር! ይኼውልህ ይቺ ናት የኔ ሀገር!
ይልቅየው ቤተመዘክር ግበና፣ የሠረቃችሁትን ሁሉ የመታሠቢያ ነገር
የራሣችሁ ስለሌለችሁ (የሰው ወርቅ አያደምቅ) የዘረፋችሁትን ከኔ ሀገር
አንድ በንድ ራሥህ እጢነው እኔ ስለሰዋ ከምናገር።
በፍቅረ—ትግሥት የተጠረዘውን፣ አገሰብጠው መጻሕፍቱን በዓያቶችህ
የተበዘበዘ የተዘረፈውን
የሥደት ምዕተ—ዓመታትን ጥሦ ከትውልድ ትውልድ የተሰለፈውን
መርምረው እሥመርምረው የፍሬ—ሐሣቡን ምጥቀት
የፍልሥፍናውን ወርድና ሥፋት፣ የቅኔውን ውበትና ጥልቀት።
ሥዕሎቹንም የብራናውን አንድ በንድ እጢናቸው
ሌላ በታ የማይደገሙ ወርቂናሌ ኢትዮጵያዊ ናቸው።
ገምግመው እሥቲ በይንህ የእጅ ብልሃት እሠራሩን
የዘውዱንና የጥሩሩን፣ የራሥ—ቁሩንና የአክሊለ—ክብሩን
በዘመናት ሕሰዊአቸው ውሥጥ፣ እጋዕዘተኪነቶቹ የተጠበቡትን
ጌጣገጡን ሲያንቆጠቁጡት፣ የመረመሩ ያሠቡትን።
አገሰብጠው ንዋየ—ቅዱሣቱን፣ ጽናውንና ጽዋውን፣ ጻሕሉንና መሥቀሉን
ከበሮውንና ሥዕለ—ቅዱሣኑን፣ ሽኹራውንና ናብሊሱን እንዲሁም
ፀናጽሉን።

ሥርዐተ—ዐልበ፣ ቅጥ—የለሽ፣ ወግ—የለሽ፣ የሜዳአህዮች እንምሠልህ
ዘንድሮ ቢውጠንም መዓት
አሁን ዘመኑ ቢያልፍበትም ፣ በጊዜው የተሠራበት ነበረን የአስተዳደር
የጦር ማረግ ተዋረድ ሥርዓት፤—
ከንቲበ፣ ፀሐፊ—ትዕዛዝ፣ ብላቴን—ጌታ፣ በጅሮንድ፣ ባሰምበራስ፣



ቀኛዝማች፣ ደጃዝማች፣ ፊታውራሪ፣ ራሥ፣ ዓቃቤ—ሰዓት።
የየብሔሩ የመተዳደሪያ ደንቡ ልዩነት፣ ሌላውን ብንተወው የአርሞ
ሕገበቼ የገዳ ሥርዓት ብቻ
የዲሞክራሲ መሠረቱም ጣራውም ነው በዘመኑ ያልነበረው እቻ።
ከናንተ አፍ ውሥጥ የማይወጣው የፍቅር እጠራሩ ብዛቱ፣ የቀልምጫወ
ዐይነቱ
እቲዋ፣ እታለም፣ እታበበ፣ ሸንኮሬ፣ እቴሜቴ፣ እበዬ፣ ወንድም—ጋሼ፣
ጃሪ ሥንቁ፤ ጃሪ ሥንቱ፤
የትዳሚው ሥርዓትና የቀሣውሥቱ ሽብሸበ፣ የፀናጽሉና የመቋሚያው
ውዝወዛ
የደብተራው መረዋ ድምፅ፣ የካህናቱ ሽብርቅ አልበሣት፣ የጽናው ዕጣ
መዐዛ
የዲያቆናቱ ቃጭል ልሣን፣ ወርቀዘበ ካባቸውና እክሊላቸው፣ ብርቅርቁ
ባለመርገፍ ዣንጥላ፣ የከበሮው ድልቅልቅታ
የታቦቱ ብዛትና ሥርዓተ—ዑደቱ፣ የታቦቱ ዘፈንና ግጥም፣ የወይዛዝርቱ
ዕልልታ
በዚች ምድር የሌለ ትዕይንት፣ ከሌላ ከዋክብት የተቀረሠ እውነታ!
ሀገሬን ብርቅዩ የሚያረጓት የደብራሆም ወዮዓለም የጸበሀ ሙዚቃ የጎህ
የእድር ጥሩምበ
የእዝማሪውና የእረሆው ፈጠራ ግጥም፣ የእረኛው ዋሽንት እንጉርጉሮ
ከምበ እምበ።
እንደ ፏፏቴ የሚፈስው፣ የነ ሃጂ መንዙማ
እረኛው ዐጥ ባለበት ውድቅት ሌት በንጋት ዋዜማ
ወደ አላህ፣ ወደ ረቢ ያም ሕላ፣ የመጅሊሱ ሁኔታ
የሊሊቱ ዱዒ በሚርቃና ሲመታ
አየር ሰንጥቆ ሲሰረቀረቅ
ልብን አብሮ የሚያስመታ፣
የዐሰህ አከበሩ ልብ የሚሠረሥር የንጋት ዜማ
ከመሥጊድ እናት ዐየር ሠንጥቶ የሚሠማ
የእሥሰሞች ሺኮች የወዳጃ ዝየራ
የግጥሙ እወራረድ ሲገበ ሐድራ።
የት ፀይተሃል እሥሰምና ክርስቲያን ተቻችሎ፣ ተጋብቶ፣ ተዋልዶ
ሲኖር በፍቅር እየተበበረ «ሀገር የጋራ፣ ሃይማኖት የግል» ብሎ ተዘምዶ?
«መሐመድ ገብረኢየሱስ፣ ገብረክርስቶስ አሊ» ተብሎ በሥሰም፣
በክርስቲያን ስም እየተጠራ
ከኢትዮጵያ ሌላ የት ገጥሞሃል፣ እሥለምና ክርስቲያን ሲተኩስ የሰላም

ደመራ ገ

አንተ የራሥህ ጨዋታዎች እንዳሉህ እኛም አሉን ብርቅዬ
የምንጫወታቸው በየተራ
ዒላማ ተኩስ፣ ሰንጠረዥ፣ አደን፣ ቅምምጦሽ፣ ምክት፣ ውሃ ዋና፣ ገበጣ፣
ተለቲን፣ ኾረ ሥንቁን ልጥራ?
በሌላ ዓለም የማይታይ ፀሎትና ምልጃ፣ ወደ አርያም ዝመራ
በክራር ሰንጎ ዜማ፣ በማሲቆ መዲና፣ በበገና ሰሰምታ ድርደራ።
የገናው ጨዋታ ዐይነተኛ ባሕል፣ ሕጉና ልማዱ የእባንዴራ
የጉግሥ ፍልሚያው ቅልጥፍና፣ የግልቢያው ጥበብ ለዛ ሰንጎ መገኑ
እያሰፈራ
የሥምሥማው እፁብ ፈሲጥ፣ የደንገለሣውና የሽምጡ ኪን፣ የፈረሱ
ረቂቅ ደንኪራ
የመሪዎቹንና የአበጋዞቹን በሞች የሚጋሩት የፈረሶቹ ልዩ መጠሪያ፣ አባ
ጃሂድ፣ አባ ጤና፣
አባ ሠይጣን፣ አባ ነፍስ፣ አባ ግርሽ፣ አባ ቀማው፣ አባ ደኘው፣ አባ
በዝብዝ፣ አባ ታጠቅ፣ አባ ዲና።
የሚነሽጠው የጃግና ፉከራው ታንከን በጎራዴ የሚያሰጨፈጭፍ፣
የሚያርበደብድ ሀገር ወራሪን
የሐርበኛ ነዛሪ ሽሰላው መስኩሜን ለውጊያ ከገደም የሚያስወጣው፣ ደፋር
የሚያረገው ፈሪን
የክራር የፋኖ ግርፋ መጽሐፉንና ብዕሩን አስጥሎ ጋሻና ጦር የሚያስይዘው
ተማሪን።
የመርደው አረዳድ ዘይቤ፣ የእልቃሾቹ ሴቶች ልብ ነኪ ግጥሙ
ስሚወዱት ፍቅርን ስመግለጽ ተዝካር ማውጣቱ፣ ዐርበውን፣ ዓመቱን፣
ሠባት ዓመቱን፣ ስማክበር መድከሙ።
የሠርግ ድግሥ ዝግጅቱ ፣ የበርበሬ ቅንጠሣው፣ የጊሸ ወቀጣው፣ የእሸሮ
አቶሳሉ
አደቋቆሉ፣ የቅመሙ፣ የብቅል አበቃቀሉ፣ የጠላ ጥንሠሣው፣ የጠጅ
አጣጣሉ፣



ግና ሠርጉ ሣይደርስ ሽርጉዱ ማስደሠቱ፣ በዓል በዓል መሽተቱ ሣር ቅጠሉ
የሙሽሪት በጠጅሣር መታጠኑ እንስስላ መሞቁ፣ ፀጉር መሠራቱ፣
ማጌጥ፣ መዘየን መኳኳሉ።
የቤተዘመድ ጉድጉዱ፣ ውሥጥ ውሥጡን ደሥ እያለት ሳይ ሳዩን
ማልቀስዋ ሙሽራዋ
ባልንጀሮችዋ ከብበዋት አይዘሽ ሲልዋት፣ ሲነግሯት ሁሏም እንደምታገባ
በየተራዋ፣
መልሠው ደግሞ ሲሏት
«ባልንጀሪት ሥሪ መደብ፣ ሥሪ መደብ
እንግዲህ ቀረ መደበደብ።
ባልጀሪት ሥሪ ጉልቻ፣ ሥሪ ጉልቻ
እንግዲህ ቀረ የናት እንጎቻ።
ባልጀሪት አይበልሽ ክፉ አይበልሽ ክፉ
ሁሉም ያገባል በየወረፉ።
መሄድዋ ነው መሰናበትዋ ነው
ችሰው ምንድነው?
የወይናበባዩ ወይፍ ናት
እሷስ ያለኛ ማን አላት?
የወይናበባዩ ዘንጋዳ
ወልዶ እሣድጎ ሰበዳ!»
ደሥ ጥሎ ውሥጡን በቂጤማ፣ በሥጋጃ በግምጃ፣ በበበ-ምንጣፍ አስጊጦ
እንደደመራ
በሩን እናሥገበም ብሎ ሙሽራውን ማስቸገሩ፣ የእድምተኛው ሎጋሽበ
ጭፈራ
ሽንጣ ከፍቶ ተኩሣትሮ በጥንቃቄ ጌጣጌጥ አልበሣት ቆጠራ
የሙሽራ ሥም አወጣጡ፣ የሚዜ ውረፋውና ሽቱ መራጨቱ
የናት ያባት ጭንቅና ደሥታው፣ የዘመድ አዝማድ የጎረቤት ምርቃቱ
የከበሮው አደላለቅ፣ የውዝዋዜው ውበቱ፣ የዘፈን የግጥሙ እንጀት
መብላቱ
የመልሥ ጥሪው አበዛዙ፣ እንደ ልዕልት ልዑል እየተካደሙ መሞሸሩ

በጫ ጉሰ ቤቱ
አንተን የሚያሥቀናህ ነው ይሄ ሁሉ ትርዒት፤ ይሄ አንተ የሌለህ
የበሕል ክምር ሐብቱ።

ምን? «ወደ ኋላ የቀረ ነው?» ታዲያ ወደ ኋላ የቀረ ነው ካላችሁ
መድፍ የሚያከክሉ ከሜራዎች ተሸክማችሁ መጥታችሁ፤ ሳይሮፕላን
ለሆቴል ከፍላችሁ
ሥጋ እንዳየ ጅብ እየተጠራራችሁ፤ በየድግሡ በየበዓሉ በታ
እየተሯሯጣችሁ ለምን ታፈጣላችሁ?
ለምን ፎቶ፤ ሲኒማ ታነሱታላችሁ? አዎን ለምን አፋችሁን ከፍታችሁ
ትመጣላችሁ?

ፍታው እስቲ ከቻልክ፤ የንጥር፣ የጥልፍና የሸማኔ ጥበብ ውሉን
የወርቅ፣ የብርና የነሃስ አምበሩን፤ የአልበውን፤ የማርዳውን፤ ያንገት
ሐብሉን
የሸሸበውንና የሸሸሉን፤ የጠልሰሙንና የድሪውን፤ የዝማሙንና የፈርጡን፤
የአልማዝና የሉሉን
የጨሌውንና የደቃውን፤ የጉትቻውንና የቀሰበቱን፤ የከፈይ ልበልማውን
የሀር ድጉንና የጃኖውን፤ ያንበሣና የነብር፤ የግሥላ ለምዱን፤ የበለወርቅ
ጫማውን
የእጥፍ በርኑማውን፤ የካበውን፤ የኩሪውን፤ የወለባውንና የድርቡን
የአሸንክታቡን፤ የበለጥበብ ኩታውን፤ የሀር እግር ሹራቡን
የእግር የወርቅ ድኩቱን፤ የሀር ዓይነ-ርግቡን
የባለወርቅ እጫዋቹን ጥሏ፤ የጎበዝዝት፤ የቀነጃጆቱን ቀሚስ የእጅ
ሹራቡን
የባሕረጃን እቃውን፤ በወርቅ ጉብጉብ ያበደውን ያንበሣ ጋማና ጎፈሩን
በመከሽ ጥልፍ የተዋበውን፤ የዝናርና የሽጉጥ ማኅደሩን
የበለብር ጣፋ ጋሻውን፤ የባለጥልፍ ቀሚሱን
የባለወርቅ ሙጣ ሎሚታ ጎራዴ የባለአውራሪሱን፤ የጃግና ሰይፍ ድጉሱን
ሥሲሚውንና መረሸቱን፤ ጥልፍ ዕቃውን፤ የበቅሎ የፈረሱን



የሱቲ፣ የግስሥና የጃዊ ልብሉን።

እናንት ጊታር፣ ቤዝ ጊታር፤ ቸሎ፤ ቨዮሊን፤ ፍሉት፤ ድረም እንደላችሁ
ሁሉ
እኛም አሉን ክራር፤ በገና፤ ማሲንቆ፤ ዋሽንት፤ ከበሮ፤ እታሞ፤
እምቢልታ፤ ቱልቱላ፤ መለከት የሚባሉ።
አዎን ተደርድሮ በያይነቱ አበተውለው ንዋየ-ማኅሌቱን
የኢትዮጵያን ልጆች ብልሃት የጥበቡን፤ የኪነቱን።

ምናልክ? ምን ዋጋ አላቸው? እንግዲያው ዋጋ ከሌላቸው
በማይበገር ግምብ አጥራችኋቸው
በአንዳች አይፈታሽ ቁልፍ ዘግታችሁባቸው
ከዐይን ብሌን ይበልጥ እየተንከባከባችኋቸው
ለአእላፍ ጎብኚዎች በኩራት እያሣያችኋቸው
ታዲያ ለምንድነው ገንዘብ የምታከብቱባቸው?
እንግዲያው ለምን አትመልሡልንም ዋጋ ከሌላቸው?

ክማረህ ብረር ወደጥንታዊቷ ሀገር ውጣና ከለህበት ኋዳ
በድህነትና በጦርነት ብቻ የምትጠራ አለመሆኗን እንድትረዳ።
ቢሸህ ከላሊበላ፤ ብደሻህ ከአክሱም፤ ከጎንደር፤ ከሀረር ጀምርና
ብርቅዬ ሕንፃዎቿን፤ ሐውልቶቿን፤ ግንቦቿን፤ ዋሻዎቿን፤
ቤተክርሥቲያኖቿን፤ ዜፋኖቿን፤ መቃብሮቿን መርምርና
ከመሥዕ እስከአዜብ ከባሕር እስከ ሊብ
ተጓዝና፤ ኢትዮጵያዬ እንደሆነች የሥልጣኔ እንቀልባ
ይገለጥልሃል የዚያን ጊዜ ዘሰለም ለማኝ እንዳልነበረች
በርሀብና በዕልቂት ብቻ የምትታወቅ የቆረቆዘች ኋላ የቀረች።

በትምህርታችሁ እንደሁ ኩራትህ
በሊቆቻችሁም እንደሁ ትዕቢትህ
የኔም ሀገር አለች፣ ነበራት ከንተ ሀገር ቀድማ ጥንት

የራሥዋ ዐይነት ሥርዓተ-ትምህርት፣ የራሥዋ ፀይነት ሊቃውንት።
ልበ አንተ የራሥህን ዩኒቨርሲቲ ከፋፍለኸው
ለኩል እፍ ሜዲሲን፣ ለኩል እፍ ሚውዚክ እንደምትለው
ለኩል እፍ ገራመር፣ ለኩል እፍ ፖይትሪ
ለኩል እፍ ፊሎሦፊና ቲወሎጂካል ቢሚናሪ
እሥዋም ዩኒቨርሲቲዋን ትለዋለች እንደቤትዋ አጠራር፣ ሣይሆን እንደጎረቤት
የንባብና የጽፈት፣ የዜማና የቅኔ፣ የብሉያትና የሐዲሣት፣ የሊቃውንትና የመለፊ-መነኮሣት ትምህርት ቤት።
አንተ የራሥህን መምሕራን እንደምትለቸው ሌክቸረር
አሢሥታንትና አሦሤት፣ እንዲሁም ሙሉ ፐሮፌሠር
እሥዋም ትለቸዋለች የራሥዋን ምሁራን
ደብተራ፣ መጋቢ ብሉይ ወሐዲስ፣ ቀኝና ግራ ጌታ፣ ለዐከ መዘምራን
ሊቀ-ጉባዔ፣ ሊቀ-ሊቃውንትና ንቡረ-ዕድ፣ ሊቀ-ጠበብትና ሊቀ-መዘምራን።

በጣም ብዙ ትምህርት አለ፣ እናንተ ነጮች የምትማሩት ከኛ
በሰብዓዊ ርኅራኄም ቢሆን እንበልጣችኋለን እንጂ እናንተ አትልቁም ሆናችሁ ብቸኛ
ጊዜ ለናንተ ገንዘብ ነው፤ ግዜ ሕይወት ነው ለኛ።
ሕጻናትን ማሣደጊያ፣ የታመመን ማስታመሚያ፣ የታሠረን መጠየቂያ፣ የተንገላታን ማጽናኛ
እዎን ጊዜ ገንዘብ አይደለም፤ ጊዜ የመሥዋዕትነት ዘመን ነው ለኛ።
እግር የጣለውን እንግዳ፣ «በሞቴ ብላ፣ ጠጣ!» ብሎ፣ ካልተመገበ መቀየሙ ቅር መሠኘቱ
እንደናንተ እንግዳን በደረቁ፣ በውሃ፣ በሻሂ ብቻ አለመሸኘቱ
የጥዋውን ተቀራርቦ መጠጣቱ፣ የደቦ አርሻው የትብብሩ
በሱቅ በባንክ ሣይመኩ፣ በጎረቤት ተማምኖ ዕቃ መዋዋሱ ገንዘብ መበደደሩ
እንሥፍሥፍነቱ፣ ለበዕድ ለዘመድም መድረሱ በችግሩ



ለንድ ቀን እንኳ ያወቁትን ሰው ቢለዩት፣ በግርነት ሆድ መባባቱ
እንገት ለንገት ገጥሞ ተጠማጥሞ፣ መንሠቅሠቁ እምባ መራጨቱ
ወለጅ እናትን ሳይቀር በ«ባይበይ!» ቀዝቃዛ አለማሠናበቱ
በውጭ የሚገባን ሰው አክብሮ «ኖር!» ብሎ በተቀመጡበት መነሣቱ
መደኂጎሙ፣ መጎራረሱ፣ እንቺ ትብሽ አንተ ትብሉ የሠለምታው ሥነሥርዓት፣ ታለቅን መታዘዝ ማክበሩ
እንደናንተ ደካማ ወለጆን የእርጌዎች መሠብሠቢያ ግቢ ውሥጥ ሣይጥሉ በቤት መጦሩ።
የኛ አረጋውያን ደግሞ ጥለ-ቢሥ፣ ለዘ-ቢሥ አይደሉም፣ የሚታፈሩ ናቸው እንጅ የሚከበሩ
ሽበታቸው ራሱ ሞገሥ አለው፣ ከፋቸው ማር ጠብ ጠብ ይላል ሲናገሩ።
ወጣቶችም በበበሬታ ያደምጧቸዋል እንጅ እንደናንተ አይንቋቸውም ሲመከሩ ሲዘከሩ
ልብ በደሥታ ይጥለቀለቃል፣ ዐይንም ተሥፋ ያገኛል እነሱ ምንም ባይሠሩ ብቻ እንደ እድባር እንደጥላ በእጠገብ በዙሪያ ሲኖሩ።
በኛ ዘንድ ያሰው አዜር ማየት፣ ይሉኝታው፣ መግደርደሩ ማግደርደሩ
ያሰፈርማ ያለጠበቃ፣ በእምነት፣ በመሐላ፣ ብቻ መዋዋሉ
ያልወለደችትን ልጅ ጡት አጥብቶ፣ እንደራሥ ልጅ ማውረሱ፣ ለደረጃም ማዋሉ
በምድር ባለገኘው በሰማይ እቀበለዋለሁ ብሎ፣ ለተቸገረ ውለታ መዋሉ
የራሥ ወለጅ ያልሆኑትን ደካማ፣ እንደግል ወለጅ እፍቅሮ መቀበሉ
የተጣሉትን ማስታረቁ፣ መሸምገሉ እንዲቀር ቂሉ
እንድ ጥጋትን ሰሠብት መካፈሉ፣ ያገኙትን አብሮ መቋደሱ
ድንጋይ ተሸክሞ ማረኝ ሲል፣ ራርቶ መማሩ፣ የበደሉትን መካሱ
አወደድርና ሕዝብህን ከሕክዝቤ፣ ይለይለት የማን እንደሚልቅ ነፍሱ።

የኛና የናንተ ልዩነት የሚያልቅ አይደለም እልፍ ጊዜ ቢዘረዘርም
እኛ በሠጠን እንሠጣቸዋለን እንጂ፣ ለወለጆቻችን ገንዘብ አናበድርም
እነሱም ያለቸውን ይቸሩናል እንጂ፣ ዕዳቸውን ሰመክፈል እንቸገርም
እንብለ እንጠጣ ብለን ወደጃችንን ወደሆቴል መርተን

የራሣችንን ሒሣብ ብቻ ከፍለን እንነሣም፤ ተጋበዙ ብለንም ጠርተን
እንደናንተ ምግብ መጠጥ ይዛችሁ ኑ እንልም፤ እናበላስን እንጂ እኛው
ሠርተን።
ሕፃናት ልጆቻችንን ደፍረን አበላሽተን፣ እኛ ራሣቸውን በየጉረኖው
እንቀብርም
እንደናንተ ቤት በኛ ቤት፤ ሴቶ ልጅ ሴትን አትገልብም
ወንድም ልጅ የወንድ ልጅ ጆርባ ላይ አይጋልብም።

ርግጥ እንከን የለንም አልልህም፤ በሤራ፣ በክህደት፣ በሐሜት፣
በአሉባልታ፣ በራስ ወዳድነት ተሞልተን በትዕቢትም ተወጥረን
መሠረነት፣ በሩት፣ አድር–ባይነት፣ ሸፍጥ፣ ጭካኔ፣ ምቀኝነት፣ ትጥፈት፣
ሁሉም አለን በደርዘን እንጨርሰውም ዘርዝረን
ደሩ ግን በዘመናት የሥቃይ ኑሮአችን ምክንያት ይኼ ሁሉ ጉድለት
ውሥጣችንም ቢኖረን
ገራገርም፣ የዋሃንም ነን እኛ፤ በብዙ በሕሪያችን እግዜር እንደፈጠረን
የቀረን
ርሀብና የርሥበርሥ መተላለቅ አርግፈውን ዛሬ ከፉኛም ቢቾግረን።
ርሥበርሥ እየተዋጋን፣ ተፈጥርን እንደመዋጋት ተባብረን
አጥፍተን እየጠፋን፣ እውድመን እየወደምን ምንም ዛሬ መዘራ ቢወረን
ወትርስ ትልቅ ሕዝብ ነበርን ጠላታችን ሣይቀር ያከበረን።
ምን ብንራብ ብንዋረድ አሁንም ኩሩ ሕዝብ ነን እስተውለን
በእጆግችን ብቻ ቀርተን፤ የምትዘሰረንን ምጽዋች ልንቀበል ተከልኩለን
ተሥገብግበን እንራኩትም፤ ተራችን እስኪደርስ በትግሥት እንጠብቃለን።
ጠኔ ይዞን እንኳ፣ «አንተ ትብስ፤ እንቺ ትብሽን» እናውቃለን።

ወይ እስመተዋወቅ፤ አለመተዋወቅ ነውኮ ነገሩን ያጠፋው
በቀለማጅ ጋዜጠኛ ተለብ ነው እንተማ ሁስንተናህ የተነፋው
ካታለምጥ የዋጥከውን ወሬ ነው፤ እንተማ መልሠህ የምትተፋው።
ሎርነት እያከራም እንጅ ሎርነትም ከመሠለህ ቀምነገር
እንደለግ ዝም ብለን አልታረድንለችሁም፤ ለነጭ አልተንበረከክትም የኔ

ሀገር።

ነገርን የሚያነሣው መቼም ነውና ነገር

ሰመሆ ኑ እናንተ እነማን ናችሁ? ጠይቀኝ ካልከስ እስቲ እንነጋገር

የመጻሕፍት መጽሐፍ በሆነው፣ በመጻፍ ትዴሥ ስለናንተ የሚነገር

ከግዜር አፍ ፈልቶ የወጣ፣ እሰወይ አንድ እንኳ ነገር?

እግዜር እንደ ኔ ሀገር፣ ሠበ ጊዜ ይጠራታል ያንቺን ሀገር?

ጭራሽ ገብታለች ወይ ያንተ ሀገር፣ እምሰከ መዝገብ ውሥጥ እንደ ኔ ሀገር?

እኮ እናንተ እነማን ናችሁ? እንነጋገር ካልከስ እሺ እንነጋገር!

እኮ በምንህ ታብየህ ነው እንደዚህ የምትነፋ ደረት?

ሰለታጃብክ ነው እንደ ጭሥ ማምባ በሚበጣጥስ ብረታብረት?

ስለተከበብክ ነው እንዴ እፍ ቢሉት እንደወረቀት በሚበታተን ቀውላላ ሕንጻ?

ሰውን እንደሠርዱን እጭቶት እሥረኛ እድርጎት፣ ከጎረቤቱ በሚያከራርፈው የሆነ ቢመስለው ነፃ?

እጽዋትንና እራዊትን በሚያወድም፣ ነቀርሣ በሚናኝ የፋብሪካ ቅርሻትና ትፋት?

በፕላስቲክ ምናምንቴ ቶሣቁሥ፣ ውሃን፣ ዐየርን በሚመርዝ ቁሻሻና ክርፋት?

እሁን ተሠለጠንኩ ተብሎ ነው ይኸ ሁሉ ጅነና? ድንቄም ሥልጣኔ!

የመንፈስ ዝቅጠትን፣ ብቸኝነትንና ራሥን መግደል የሚፈለፍል ሥልጣኔ ይቅርብኝ እኔ!

ርሥበርሥ የሚያባላ፣ ወላጅና ልጅን የሚያናክስ ሥልጣኔ ይቅርብኝ እኔ!

ቶሣቁሥን እምላኩ እያደረገ፣ ሰው ፈጣሪውን እንዳያውቅ የሚያደንቁር ሥልጣኔ ይቅርብኝ እኔ!

ሰደሰር ብሎ እንዴ ሌላውን እንዲያርድ የሚያደርግ ሥልጣኔ ይቅርብኝ እኔ!

የሰውን ልጅ ክቡር ገላ እያዋረደ ወሢብን ፋብሪካ እርጎ የሚያሸቅጥበት ሥልጣኔ ይቅርብኝ እኔ!

ደበውን፣ ሥጋውን፣ እትክልቱን፣ መልከሙን ምግብ ሁሉ መርዝ ቀላቅሎ

የሚቸረቸር ሥልጣኔ ይቅርብኝ እኔ!
ፀያፉን ከሠናይ፣ ከፉውን ከበጎ የማያስለይ፣ ሰውን ከብት የሚያደርግ
ሥልጣኔ ይቅርብኝ እኔ!
ጭከኔን፣ መናፍቅነትን፣ ጥለቻን፣ ምግባረ-ቢሥነትን፣ ቀውስነትን
የሚያስፋፋ ሥልጣኔ ይቅርብኝ እኔ!
የሰውን ልጅ ዘርና መለውን ሕይወትን አጥፍቶ ሲጠፋ የቀረበ ሥልጣኔ
ይቅርብኝ እኔ!
የኔዋ ድሀ ሀገር ግን በእልፍ አእላፍ ዘመናት ሥልጣኔ
ሬትቃ በቤት ውሥጥ ምጣኔ
ባለሙያ ልጆቿ የሚቀምሙት ምግብ እንዴት እንደሚጥም
ትመሠውና ከያይነቱ፣ ከናፍርህን ለሣቸው፣ ጣቶችህንም ቆርጥም።
ሞከረው አሥቲ የዶር ወጡን፣ አልጫውንና ቀዩን፣ ምንቸትአብሹንና
በዘናውን
ሰሰሒውንና ትንጪውን፣ ሽምብራዐሣና አዚፋውን፣ ምጥኑንና ክኩን፣ ሽሮ
ወጡንና ጭቅናውን
ክትፎውንና ቶሞውን፣ ጭከና ቷንጣውን፣ ሰብሰቡንና ጥብሥ ሥጋውን፣
እምቢሸና ጢጢብባውን።
ተጎንጭሰት ሰብርዙ፣ ከሸከቴውና ከበተሒው፣ ከከረፋውና ከጠላው
ከግፋና ከወይን ጠጁ፣ ከፊልቴፋና ከከቲካላው።
ልብ በለው አሠራሩን የሥልጃውን፣ አቀማመሙን የበርበሬውንና የምጥኑን
ሽሮ
የአዋዜውን፣ የድልሁን፣ የሚጥሚጣውን፣ ኧረ የሥንቱ ተዘርዝሮ!
የንጥር ቅቤውን ጣም ሣህን የሚያቢልለውን፣ ሽታው እጅ ላይ እንደ
ናርዶስ ለወራት የሚቀረውን
መዐዛው በጋራ ተጠምጥሞ አገር ላገር በዐየር እየናኘ የሚዘረውን።
ድሥት ውሥጥ ጥሬ ቅቤ፣ ያልታመሠ በርበሬና ጨው ሞጅሬን
ወጥ ሠርቶን ጨርሰናል እንዳም እኛ፣ እናጥመቀለን ሺ ትመግቀመም
ጨምረን።
ምግባችንን እናጣፍጠዋለን በነጭ አዝሙዱ፣ በእበ-ሱዳኑ፣ በበሦብላው፣
በከረሪማው፣ በጤናዳሙ፣ በእርዱ፣ በድምብላሉ

በቅርንፉዱ፣ በከሙኑ፣ በቀረፋው፣ በዝንጅብሉ፣ በጦሥኙ፣ በፈጦው፣
በሱፉ፣ በኑጭ ሽንኩርቱና በሔሱ።
እ? ትሥቅብኛልህ፤ ምነው አንቺ! ርሀብ ቢጠናብን ምንም
መሠለህ እንዴ ያጣነው ሙያውንም?
ደሩ ግን እውነትክን ነው፣ ዘሬግ ምን እፍ እለን
ትራፊህን እየተቀራመትን፣ ያንተ ተመጽዋች ሆነን ቀጥለን።
እ? በትክክል ነው የለማሁህ? አንተም እንደኔው እኮ ነህ ነው ያልከኝ
እሁን
እሠይ! ልክልኬን እንደሱ ንገረኝ፣ ብያለሁና አንተን ልሁን!
ሥረ-መሠረቴን፣ ማንነቴን ባለማወቄ ራሤን ንቄ፣ አንቱን ለመሆን
ጥሬያለሁ
የሠለጠንኩ መሥሎኝ ደንቁሬ፣ እንደጦጣ ልክ ጅዝህ ተፍጨርጭሬያለሁ።
ተሣክቶልኝ ሙሉ አንተንማ ብሆን፣ አልሆንኩም እንጂ በማን ዕድሌ
እኔስ ያንተ ግማሽ ነኝ፣ ነፍሴ የገማ ጉራማይሌ
ልቤ በረደ ለውጡ ሲ፣ የበሠበሠ እንጎሌ
ደሞ እሬን ሞልቼ አንተን መተቸቴ፣ ደንዘ ዝጎ እቀሌ!
የኢትዮጵያንስ ሕዝብ በአንደኔ ዐይነቱ ዐረመኔ እትለካው፣ እታቀልለው
እኔ በመቅለሌ
ያን ሸጋ ሕዝብስ እትመዝነው፣ በእንደኔ ዐይነቱ ምናምንቴ፣ እኔን
በመሠለው ሰው-በሌ
ያንን ገራገር ክቡር ሕዝብስ እታወዳድረው እኔን ከመሠለው እልባሌ
እዎን ያንን ባለታሪክ ሕዝብስ አትናቀው ገምተኸው በእንደኔ ብጤው
ወር-በሌ።
እንተም ከትቢትህ፣ ከንቀትህ በቀር
እለህ እንዳንድ ነገር የሚፈቀር
እታውቅም ብዙ ቂም-በቀል
ተቀናቃኝህን ከነሥሩ መንቀል።
ተጣልተህ፣ ተቧቅሠህ፣ ትችለለህ ቶሎ መታረቅ
ሂሥ ሲቀርብብህ ራሥህን ያለማጣ ማረቅ።
የምታውቀውን እውቃለሁ፣ የማታውቀውን ግለት እላውቅም

እንደራስ ማደር፣ አለመንጠራራት አለ አቅም።
የበለጠህን ከማጥፋት፣ እሱ ላይ ለመድረስ መወዳደር
የቀደመህን ከመጎተት፣ ልትቀድመው መንደርደር።
ለሥራ መትጋት፣ የቀጠሮ ሰዓት ማክበር
ለእምነት ሽንጥን ገትሮ፣ መስዋት ያለመሸበር።
ከጃርቧ እያሙ እያልጎመጎሙ ከማነጋገር
እቅጩን አፉትለፋት እርፍርጦ መናገር።
ባላሥፈላጊ ይሉኝታ አለመጠፈር
ትክክለኛውን በግልጽ ማድረግ ይዞ ፈር።
መሸለም የሚገባውን መሸለም፣ መክበር የሚገባውን ማክበር
መደመጥ የሚገባውን ማዳመጥ፣ ትብብር ከሚገባው መተባበር
ተወያይቶ ችግር መፍታት፣ ይቅርታ ሲጠየቁ መማር
ይሽን ሁሉ ካንተ እማራለሁ፣ አንተም ሌላውን ከኔ እንደምትማር።
በርግጥ የማይካዱ፣ አንዳንድ መልካም ባሕርያት ውስጥህ አሉ
እንደኔ ሐብታም በሕልና ሬጅም ታሪክ ባይኖርህም ቅሉ።

ታሪክ ምን ይረባል አልክ? እሱማ ልክ ነህ፤ ታሪክ ምን ፋይዳ አለውና
ታሪክ አይበላ፣ ታሪክ አይጠጣ ምን ቢሆን ገናና
ስለትናንት ማን ግድ አለው? በዛሬ ብቻ ነው ሁሉን ነገር የሚለኩት
ስለዚህ ነው ታሪክ–ቢሥ ዳንዴዎች፣ ዛሬ ታላቅ ተብለው የሚመለኩት።
አንተማ ምን አጠፋህ፤ ለነዳያን መጽውት ቢሉህ ላክህ ምጽዋትህን
ለነዳያን
እኔ ነኝ እንጂ ያልፈየድኩላት፣ ቅንጣት ታህል ያልጠቀምኳት
ኢትዮጵያን።
አንተማ ቁንጣን ሲያፈነዳህ ደርሦ ሕሊናህ ሲሆንብህ ከታፋህ
በሕሊናህ ክትፊት ለመዳን፣ «ሠብዓዊነትህን» ለማሥመሥከር፣ ተዘክርክ
ቆንጥረህ ከትራፋህ።
አዎን እኔ ነኝ ያልረባሁሽ እናት–ዓለም
በጭንቃሽን ያልተካፈለሽ እንደኔም የቂወሽ የለም።
እኔ ራሥ–ወዳዱ እንቺን ለጠኔ ትቼ፣ ሕይወቴን ላሸሽል ተግቼ።

ጆሮዬን በሠም ብደፍንም ዐይኖቼን በሙጫ ዘግቼ
ውርደት ብቻ ነው ያገኘሁት ተደሥቼም አልተደሠትኩ እንደተመኘሁት
እንደ ለማኝ ነው የተቀጠርሁት፣ ርሀብ የተፋው ነው የተለኘሁት።
ምንም ማንነቴን ልደብቀው ብሞክርም
ምንም ራሴን ልከደው ብጥርም
ያልፋፋሁኝ ይመሥል እየመጠመጥኩ ጡት–ደምሽን
ዛሬ ጡትሽ ነጠፈና አሳውቀውም ብልም ለምሽን
ቀዳ የማይፈቅ ሆኖ ግምበር የማይደበቅ ነገር
ያንቺ መሆኔን ሲረዱ ዐይንህን ይሉኛል ሳፈር።
ድሮ በጥጋብሽ ጊዜ፣ ሁሉ ያከብረኝ ይፈቅደኝ እንዳልነበር
ዛሬ እንቺ ስሳጣሽ ስለነጣሽ፣ ሁሉም በሩቁ ይዘጋብኛል በር።
ከንግዲህ ወዲህ ብክድሽ ቃል ለምድር ይሁን ለሰማይ
ሣሏፍርብሽ አልሸለሁ እንጂ ያንጀትሽ ቁራጭ ነኝ እማይ!
ጣቶቼን ጆሮዎቼ ውሥጥ ከትቼ
የቤቶች ጣራ ላይ ወጥቼ
ኢትዮጵያዊ ነኝ ብየ እጮሃለሁ
ከአድማስ አድማስ እለፍፋለሁ።
በመሏው ፕላኔት አውጃለሁ
እልፍ ጊዜ ነኝ ኢትዮጵያዊ!
አይደለሁም አሜሪካዊ!
አእላፍ ጊዜ ነኝ ኢትዮጵያ ዊ!
አይደለሁም እንግሊዛዊ!
እምአእላፍ ጊዜ ነኝ ኢትዮጵያዊ!
አይደለሁም ፈረንሣዊ!
እወቁት ነኝ ኢትዮጵያዊ!
አይደለሁም ጃሜይካዊ!
የአፍሪካ ልጅ ነኝ ንፁሕ ኢትዮጵያዊ!
ዛሬ ብዋረድም ነኝ ኢትዮጵያዊ!
ብራቆትም ነኝ ኢትዮጵያዊ!
ብበደድም ነኝ ኢትዮጵያዊ!

ኢትዮጵያ ዊ ነኝ የጠራሁ አፍሪክ ዊ!
በሁኔታ ተገድጄ ፓስፖርቴ ቢለወጥም፣ እኔ አልለወጥም ነኝ
ኢትዮጵያ ዊ!
ትናንት ነበርኩኝ ኢትዮጵያ ዊ!
አሁንም ነኝ ኢትዮጵያ ዊ!
እሞታለሁ ሆኜ ኢትዮጵያ ዊ!
እወቁልኝ ነኝ ኢትዮጵያ ዊ!
ንፁሕ ኢትዮጵያ ዊ ነኝ ነበር አፍሪክ ዊ!
ይ ቅርታ አርጊልኝ እናት ዓለም፣ ደሽየች ብዬ በለከድሁሽ
በሳፈርኩበት በውርደትሽ፣ በውድቀትሽ ስላልፈቀድሁሽ
ደሥታሽን ተቋድሼሽ፣ ስላልተጋራሁሽ ሀዘን፣ ስቃያሽን
ጠኔ ጉረሮሽን ሚጥ አርጎት፣ ስላልተካፈልሁሽ ሲቃሽን።
ነገ ርሀብሽ እስትጥሞ ተረት ሲሆን፣ ፀዱኛሽ ተትረፍርፎ ከእጽናፍ እጽናፍ
አለቅሦሽ ላይ ሣልገኝ እሠርግሽ ላይ ልኖር፣ ከተፍ ብዬ ከደጃሽ
ትናንት በበረርኩበት አክናፍ
እመጣክ ይሆናል፣ አፍሪተ–ቢሡ ልጃሽ
እንቺማ እናት ነሽና አይጨከንም ከንድሽ እጃሽ
አ ቅፈሺኝ እንኳን ደህና መጣህ እንጂ ጥፋ አትይኝም ከደጃሽ።
የጣር እልፃሽ አጠገብ ተገኝቼ ርሀብሽን ባላተጋራሁሽ፣ ማረኝ አናትዓለም
ሥቃይሽን እንዳሳይ ለእመንኩበትም ብቻ እንድቆም፣ ጥቂት
እንድሠነብትልሽም ብዬ ነው እንጂክ ጠልቼሽ አይደለም።

ዳሩ እንጀራ ሆኜልሽ ላታለምጭኝ፣ ሥጋ ሆኜልሽ ላትነጭኝ
ውሃ ሆኜልሽ ላትጠጭኝ፣ ወተት ሆኜልሽ ላትጎነጭኝ
በድን ርቃነሥጋሽን እንደወረሩት ዝምቦችና አሞሮች
እንዲያው በዙሪያሽ ባንዣብብልሽ፣ እምባዬን ብረጭልሽ
አጽምሽ አጠገብ እያረገድኩ፣ ፊቴን በሾህ ብቧጭርልሽ
ምን ልፈይድልሽ ደረቴን በድንጋይ ብወግርልሽ
ባይሆን እኔ ለዘር ልትረፍልሽ፣ ባይሆን ጥቂት ል ኑርሽ።
ምንም የኔ ላንቺ መቃጠል፣ እሀል ውሃ ባይሆንሽም ኢዮሄዶ

ግን እኮ እዚህም ኢዮሄ! እልልሽለሁ፣ እስቀሥልሽለሁ ለብቻዬ
ከመላው ምድረገጽ ለሥቃይ፣ ለርሀብ፣ ለምን? ለምን? ተመረጠች
ኢትዮጵያዬ!

በኃጢዓትዋ ነው ይሉኛል ቄሱ፣ መልሣቸው እንጃቴን ላያረኪ
ኃጢዓትሽ ይብስ ይሆን ከአውሮፓና ከአሜሪካ?
እግዚር ለሚያፈቅራት ነው የሚቀጣት ይላሉ ቄሱ
እባትም የሚቀጣው የገዛ ልጁን ብቻ ነው የሚወደውን እንደራሱ
ሌሎቹን የማይቀጣቸው ሰላይደሱ ነው የሱ።
እሥራኤል እግዚር የመረጠው ሕዝቡ ሆኖት
ባምላኩ ላይ በላመፀ፣ በርሀብ፣ በቸነፈር፣ በጦርነት ቀጥቶት፣ በመላው
ዓለም በታትኖት
ኋላ ግን ሕዝበ እሥራኤል ቢፀፀት ጥፋተኛነቱን ተቀብሎ
እንደገና ሠብሥቦ ነፍሥ ዘራበት፣ እንደሌላው አልጣለውም ጥሎ
ኢትዮጵያም እግዚእ ካለች፣ ይቃረቃቃል በቃሽ ብሎ»።

ፖለቲከኛውንም ስጠይቀው የራሱን መልሥ ይሠጠኛል
በመንግሥት፣ በተፈጥሮና በእስተራረስ ጥፋት ነው ይለኛል።
ባለታሪኩንም ብናገረው «ከክሱም በፊት ያለውንኪ ብንተወው ተነገር
ስለማይጨረስ
ከክሱም መመሥረት እንሥቶ እስከጣሊያን ወረራ ድረሥ
የኢትዮጵያን ታሪክ ብንመረምረው ባለፈው ሃምሣ ዓመት ብቻ
ከውጭ ወራሪ ጋር መተላለቅ፣ ርሥበርሥ መተራረድ ነው ባለም የሌለው
እቻ
የደም መፍሠሥ ታሪክ ነው ታሪክዋ የኢትዮጵያ
ታዲያ መቼ ሠላም አገኝታ ትበሸል?» ይለኛል የታሪኩ ባለሞያ።
መንሥኤው ሰው-ሠራሽ ይሁን የእግዚር ቁጣ፣ ወይም የተፈጥሮ
ሐቁ ተርበሸል፣ ተራቁተሸል፣ ደምተሸል ኢትዮጵያዬ
ምክንያት ቢደረደር አይበጅሽም ዘንድሮ።
እኔ ልጅሽ ግን እምናለሁ፣ ይኼ ቀውጢ ቀንሽ ተሸሮ

በጥጋብ፣ በብልጽግና፣ በፍቅር፣ በሠላም ተቀይሮ
ዛሬ ለርሀብና ለጦርነት ተጋልጠሽ እንደተዋረድሽ፣ ነገ እንቺነትሽ ተከብሮ
አንቺ ለመላው ዓለም የብልጽግና፣ የሠላምና የፍቅር ምሣሌ ሆነሽ
ትቢያውን ከላይሽ ላይ በትነሽ፣ ሞተሽ ከተቀበርሺበት እንደምትነሺ!

እ/ ኤ/እ 1987
ብሬመን፣ ምዕራብ ጀርመን ተፃፈ።

ሰኔ ፲ ቀን/፺፭ ዓ.ም.

ለዶክተር ፍቅሬ ቶሎሳ ፡

ከሁሉ አስቀድሜ የማክበር ሠላምታ አቀርባለሁ ። ስመጥር የሆነ ጽሑፍ ሠው በመሆንዎ በብዙ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ሥራዎችዎ ስለሚታወቁ እኔም እንደሌሎቹ ሁሉ በዚሁ ሚዲያ አውቅዎታለሁ ። እርስዎ ግን እኔን አያውቁኝም ፡ ባ[illegible]ሔኔ በኢትዮጵያ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ውስጥ ለሀያ ዘጠኝ ዓመታት አገልግዬ ወያኔ ኢት[illegible]ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ በጡረታ ላይ የምገኝ ኢትዮጵያዊ ነኝ ።

“ ነገር ቢበዛ በአህያ አይጫንም” እንደሚባለው በአገራችን ገጣሚ አባባል ላይ በመመርኮዝ ነገር ሳላበዛ ይህን ለመፃፍ ወደ አነሳሳኝ ጭብጥ እንደመራ ይፈቀድልኝ ።

በቅርቡ ማለትም እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር መጋቢት 28 ቀን 1995 ዓ.ም.( *April 6/ 2003* ) ከሰዓት በኋላ ከ11.00 ሰዓት እስከ 12.00 ድረስ አንድ እጅግ ሠፊ ለሀገርዎ ኢትዮጵያ በግጥም የደረሱትን ሥነ ግጥም በጀርመን ሬዲዮ የአማርኛ ፕሮግራም ቀርቦ እንደነበርና ባጋጣሚም ለመስማት እድሉ እንደገጠመኝና ግጥሙም በጣም እንዳማረከኝ በትህትና ለመግለጥ እወዳለሁ ። ስለዚህ ስለተዋጣ ሥራዎ ከፍ ያለ አድናቆቴንም አቀርባለሁ ።

እንደ እውነቱ ከሆነ “ ሰበቡ” ሳይሆን ስለእውነት ለመናገር ግን እንጂ ይህ ጽሑፍዎ በአገራችን ለሕዝብ አሳቢና ተቆርቋሪ መን[illegible]ሥት ቢኖር ኑሮ ወጣቱ ትውልድ እንደ “ ውዳሴ ማርያም” ጧትና ማታ እንዲያነበው “ በሥርዓተ ትምህርት” ባስገባው ነበር የሚል አመለካከት አሳድሮብኛል። ከኢትዮጵያ ውጭ በስደት የሚኖረውም ወጣት ትውልድ ወደዚህና ወደዚያ ከሚዋዥቅ ሥር መሠረቱን ጠንቅቆ በማወቅ ፈረንጆች እንደሚሉት *identity crisis* ውስጥ ገብቶ ለራሱም ለቤተሰቦቹ ም ሆነ ለአካባቢው ችግር ከመፍጠር ይታደግ ነበር ።

እንደእኔ እንደእኔ ይህ የእርስዎ ሥነ ግጥም ስለአገራችን አኩሪ ታሪክና ባህል ጥርት ባለ መልኩ በሚያውቀው አስታዋሽና ለማያውቀው አስተማሪ በመሆኑ በኢትዮጵያዊያን ዘንድ በሥፋት ሊሰራጭ ይገባል ባይ ነኝ ። ቢያንስ ቢያንስ እኔ በአካባቢዬ በዚሁ ተግባር ከመንቀሳቀስ እንደማልቆጠብ ባረጋግጥልዎት እወዳለሁ ።

በጀርመን ሬዲዮ የተሰራጨውን ይህን የእርስዎን ሥነ ግጥም ካዳመጥኩበት ቀን ጀምሮ ሙሉ ጽሑፉን ለማግኘት “ ያልፈነቀልኩት ድንጋይ” አልነበረም ። እነሆ ይህን ለእርስዎ ለመጻፍ የተገደድኩት እዚህ አዲስ አበባም ሆነ ኮሎን ከሚገኘው የጀርመን ሬድዮ ጣቢያ ፅሑፍዎን ባገኝ ባለመቻሌ ነው ። ለእርስዎ ጽሑፍ የተጠቀመው የጀርመን ሬዲዮ ጣቢያ ወኪሎች ጽሑፍዎን ቀርቶ አድራሻዎን እንኳን ሊሰጡኝ በጎ ፈቃድ አላሳዩም ። ስለሆነም የማያስቸግርዎ ቢሆን እዚያው እርስዎ በሚኖሩበት አገር ሦሥት ልጆቼ በሥራ ተሠማርተው ስለሚኖሩ ግጥምዎን ሙሉ ለሙሉ ለመረዳት ባይችሉም እንኳን በእኔ እርዳታና ድጋፍ ቀደም ብዬ እንደገለጥኩልዎት “እንደ” ውዳሴ ማርያም” ወይም እንደ “አቡነ ዘበሰማያት” እንዲያነበንቡት ስለምመኝ አንድ ቅጂ በእነሱ አማካይነት ቢልኩልኝ ምሥጋናዬ ወደር አይኖረውም ።

የሕትመቱንም ሆነ የመላኪያውን ዋጋ ለመክፈል ፈቃደኛ ነኝ ።

ሁለቱ ገለማሳ ልጆቼ አንድ ላይ ከዚህ በሚከተለው አድራሻ ይገኛሉ ፡
ፅሑፉ እንደደረሰን ለሦስተኛዋ ትንሿ ልጄ አለችበት ድረስ እንልከላታለን ።

ከላይ ባለው የልጆቼ አድራሻ ቢላኩልኝ እንደሚደርሰኝ ላረጋግጥልዎ እወዳለሁ ።
አለበለዚያ ግን የእኔ አድራሻ ፡

ስለሆነ በዚህ ሲልኩልኝ ወይም ሲያገኙኝ እንደሚችሉ እየገለጥኩ በቅድሚያ ሊያደርጉት በሚችሉት ሁሉ ምሥጋናዬን ወንድማዊ በሆነ ሥሜት እገልጣለሁ ።

የርስዎ፡

ጎስማየሁ አበበ ሸነቁጥ (አወጣላጀር)

# ዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሳ

ይህ የማነው ፍቅሬ ቶሎሳ
እንደ አንበሳ የሚያገሳ
ደረቱን ነፍቶ እንደ ዳሽን ተራራ
ማንንም ሳያፍር ሳይፈራ
በኢትዮጵያ ባገሩ የሚኮራ?
እረ ለመሆኑ ማነው ይህ ዶ/ር ፍቅሬ
ጥልቅ ፍቅር ያለው ለአገሬ
ጠቢብ ጥልቅ ረቂቅ
የኢትዮጵያን ታሪክ ከሀ እስከ ፐ የሚያውቅ
ስነስርዓቱን ባህሉን ማዕረጉን
ኃዘኑን ሰርጉን ድግሱን
መጠጡን ምግቡን ቅመሙን
የአገሩን አጥዘበና ትምህርት
የተለያየውን ሁሉ ዐውቀ
እንደዚሁ ጠንቅቆ የሚያውቅ
ምሁርና ሊቅ
ከየት ተገኘ ከየት መጣ?
ከየት ፈለቀ ከየት ወጣ?
ሳውቅ እፈልጋለሁ ንገሩኝ
የቆማችሁ ሁሉ በግራና በቀኝ
ይህና አርጋችሁ አስረዱኝ።
በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያን ሲያጎናጺት
እንደፋሲካ ዶሮ ሲገነጣጥሏት
እንዳልሆነች ሲያረጓት
ሲያዋርዷት ሲያንኳስሷት
ሲያወርዷት ሲጥሏት
አጸያፊ ስም ሲሰጧት
ከየት መጣ ለኋ የሚቆም ጠበቃ
ይህ የደራሲያን አለቃ
በሞቀ መንፈስ የሚከራከር
ከእንደበቱ በሚፈልቅ ቁምነገር
በያዘው በሰላ ብዕር
ኢትዮጵያ አገሩን የሚያከብር

አገሬ ትበልጣለች እንጂ ከማንም አታንስ የሚል
እውነት መሆኑን በሰማይ በምድር የሚምል
ይህ ሰው ያገሩን ታሪክ በጥልቅ የተመራመረ
በፍልስፍና በቋንቋ የከበረ
ሕሊቱ ንገሩኝ ከየትኛው መሬት ተቆፈረ ።
አንዳንዴ እንደ ከበደ ሚካኤል
አንዳንዴ ጸጋዬ ገ/መድህንን የሚመስል
ጽሑፉ እንደ አዱኛው ወርቁ ማሞም
የሚጣፍጥና የሚጥም
እንደ ዓለማየሁ ሞገስ እንደ መንግስቱ ለማ
የሚያስደንቅ ላየ ለሰማ
እንደ አሉላ ዋሴ እንደ አሰፋ ገ/ማሪያም ተሰማ ስንኝ
ጣመኝ ድገመኝ የሚያሰኝ
ሊሞገስ የሚገባ ገኸኛ
እንደ መልካሙ ደራሲ እንደ አቤ ጉበኛ።
"ድሀች ናት የኔ ምድር

ይህች ናት የኔ አገር"
እያለ ይህ ግለሰብ ከአንደበቱ አምርሮ
ጓደኛን አፍሶ ማንባሩን አከማችሮ
በጀግንነት ሽንጡን ገትሮ
ለኢትዮጵያ ጠላቶች መልስ የሚሰጥ
በያዘው ብዕር የሚያናውጥ
የሚያስፈራራና የሚያንቀጠቅጥ
የሚያርበደብድና የሚያራውጥ
አገሬ አይደለችም እናንተ እንደምትሉዋት
እያለ ቢሉት የሚሚገት
ንገሩኝ ይህ ወርቅ ደራሲ ከየት ተፈለፈለ
ከየትኛው ሰማይ ዱብ አለ?
"ሁሉ ፈንጂዎች
ሁሉ ሽምንሚኖች
የውበት መጋዘኖች"
እያለ የአገሩን ሴቶች የሚያሞግስ
ስሜታቸውን የሚቀሰቅስ
መንፈሳቸውን የሚያድስ
የኢትዮጵያን ሕዝብ በሞላ
ፍጹም የሚወድ በጠቅላላ
ጎጃም ሳይል ጎንደር
ሸዋ ሳይል ሐረር
ምዕራብ ሳይል ምስራቅ
ቅርብ ሳይል ሩቅ
ከዳር ነው ሳይል ከመሃል
ሳይነጥል ሳይነጣጥል
እስላም ሳይል ክርስቲያን
ወገንን ሳይለይ ከወገን
የሚንከባከብ ሁሉን አለሁላችሁ እያለ
እንደዚህ ያለ ግለሰብ ከየት አቅጣጫ ብቅ አለ?
ይህንን ለኔ ሊያስረዳ
ዘመድም ሆነ ባዳ
በአንድነት ዛሬ ይሰናዳ።
እባካችሁ ንገሩኝ ሳይውል ሳያድር
ቆርጫለሁና ለማወቅና ለመማር
ስለ ፍቅሬ ቶሎሳ ስለ ዘመኑ ታምር

በጁዎም ስለያዘው ትንግርተኛ ብዕር።

++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++++
++

ከላይ የጻፍኩትን ግጥም በጀርመን ድምፅ ሬዲዮ አቶ ተክሉ የኋላ ስሜትና ጣዕም ባለው መንገድ አንብቦታል። ይህ ለሬዲዮው ጣቢያ ውበትና ድምቀት የሰጠው ኢትዮጵያዊ የሰማው ሁሉ ያለውን ችሎታ ከማድነቅ ወደኋላ አይልም።


ግርማ ዳምጤ ሀብተየስ

Girma Damte
P O Box 600
Angwin, CA 94508
USA


August 7, 2004

ይህ ግጥም እኢአ ከ1987 ዓ/ም ጀምሮ በጀርመን ሬዲዮ ሲተላለፍ አድማጮች እንደገና መስማት እንፈልጋለን ስላሉ በተከታታይ ብዙ ጊዜ ተሠምቷል። የብዙ ኢትዮጵያውያንን ሞራልና ኩራት በማነሳሳቱም በርካታ የሀገሬ ሰዎች የምሥጋናና የአድናቆት ደብዳቤዎች ለኔና ለሬዲዮ ጣቢያው ከመጻፋቸውም በተጨማሪ የግጥሙን ግልባጭ እንድልክላቸው ጠይቀውኝ ነበር።



ዶክተር ፍቅሬ ቶሎሳ

$ 5.00